<u>ግልፅ ደብዳቤ ለአቶ ኦባንግ ሜቶ</u>

<u>ወጣ ወጣና እንደ  ሽንበቆ ሆነሳ ነገርዎ</u>

በአኝዋክ ጀስቲስ ካውንስል ወይም በአንዋክ የፍትህ ቆንስል ስም የሚያካሂዱትን እንቅስቃሴ ከሚከታተሉት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነኝ፡፡ እንደ ሲቪክ ማህበር ቦታ ና ሚናን ለይተው እየሰሩ ነው በሚል ግምትም ይበርቱ ይሎት ከነበሩት አንዱ ሆኜ ቆይቻለሁ፡፡

ታዲያ የዘሬን ብተው ይዘርዝረኝ ሆነበዎት መሰል እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጉደና ጅራት ወደ ኋላ ብለው ዛሬ እነሆ የልብዎን አውጥተው ሲፅፉ ምነዋ እርስዎ ም አንድነት እያሉ በዚያው የጠበበ የክፍፍልና ከለልተኛ ጎራ ገቡ ማለትን ተገድጃ ለሁ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባሰራጩት ፅሁፎችዎ በግልፅ እንደተቀመጠው ለሀገራች ን የተዋደቁትን ታጋዮች በአሮጌና የቀድሞ ታጋይነት በመፈረጅ ለእርሰዎ አዲስና ፍሬያማ የተጋይ መሪዎች ማለት እነማን እንደሆኑ ዘርዝረውም በስም አሊያም በአዲስና ወጣት ጥቅል ስም ሊያቀርቡልን ሞክረዋል፡፡ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄንም ማንን ይዘው ሊያቋቁሙ እንዳቀዱም ሲያቀርቡት የመጨረ ሻ ተልዕኮዎ ቁልጭ ብላ ትታያለች፡፡ አዲዮስ ሚዛናዊነት!

አላማዎ ምንድነው? ማንነትህን ለማወቅ ጓደኞችህን ማወቁ ይበቃል ይባላል፡፡ እርስ ዎ አዲስና ብቁ መሪ ብለው የሚያደንቋቸውን ስም ዝርዝር ስናነብ ምንም እንኳን ስልክ ሲደውሉ የመለሰው ሁሉ ተጠቃሏል ወይም የቀረ አላፊ አግዳሚ ያለ ባያስመ ስልም በአብዛኛው አንድም በተደራጀ መልክ የፖለቲካ ትግል ተመክሮ የሌላቸው ሲሆኑ በሌላ በኩለ ደግሞ የተወሰነ ንቅናቄ ደጋፊና አባላት መሆናቸው ምስጢር አይደለም፡፡ አቶ ኦባንግ የፖለቲካ አቅዋም ይዘው ወገንተኛ ከመሆንዎ ሌላ እያሰራ ጩ ያለው አደገኛ ሰባከ ፀረ ድርጅትነትን ነው፡፡ በድርጅት ሆነው ለሀገር የሞቱትን ወይም በድርጅት ሆነው እየታገሉ ያሉትን የቀድሞ፤የድሮ ወዘተ በሚል ተገቢውን ቦታ ሳይሰጡ ለመተቸት ከመነሳትዎ ሌላ ይህን መሰል አቅዋም የያዙና አንዳንዶቹ ም በፀረ ትግል አቅዋማቸው ሚናቸው በጥያቄ የገባውን በጀግና ወይም ንቁ መሪ ደረጃ ሊያቀርቡልን ሞክረዋል፡፡ ይሁንልዎ እንኳን ብንል ይህ የፖለቲካ ድርጅቶች ን ያገለለ ሂደትና ስብስብ አቅዋምዎ በመሰረቱ ለማን ይጠቅማል ሲባል ያው ያልተ

ደራጀውን መሪ ነን ብለው ሊሰየሙበት ለቃጡ የስልጣን ጥመኞች ወይም ለመለስ ዜናዊ ለራሱ መሆኑ አያከራክርም። ድርጅት አልባ ማንኛውም ትግል ድልን አይቀዳጅም። የአኝዋክ የፍትህ ካውንሲል ለሕዝቡ መብት መጮህ ቢችልም ለለውጥ ትግል ሚናው ውሱን ነው። ዝንብ ቢሰበሰብ መሶብ አይከፍትም ዓይነት መሆኑን መደባበቁ ዋጋ የለውም፣ ባለን ግንዛቤ ፀረ ድርጅቶች ሆነው ብቅ ያሉት ሁሉ ትግልን ሲያደናቅፉና ውዠንብርን ሲያስፋፉ እንጂ ትግልን ሲያጎለብቱ አላየንም። ለዚያውም ፀረ ድርጅትነታቸው ለሌሎች እንጂ ለሚደግፉት ድርጅትም የሚተርፍ አይደለም።አዲስ የሚሉትን ለመትከል ደግሞ ያው እጅ እጅ ባለን የቆየውን በማንኳሰስ መንገድ ሲሄድ በዝምታ ልንቀበለው የማንችለው ይሆናል።

አቶ ኦባንግ፣ በሰብዓዊ መብት ዙሪያ እንደ ማንኛውም የሲቪክ ተቋም የበኩልዎን አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ቢያተኩሩ በተሻለ ነበር። ፖለቲካውን ከፈለጉ ደግሞ በግልፅ በሚደግፉት ቡድን ገብተው በመሰለፍ ወይም የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋም መታገሉ ቀናና ሀቀኛ እርምጃ ይሆናል። በሽፋን ፖለቲካ መንጎድ ጓደኛዎ ሊነግርዎ እንደሚችለው ስልጡን ፖለቲካ አይደለም። ኢትዮጵያ ወላድ ሀገር ናትና ብዙ የፖለቲካ መሪዎች አሏት ግን እርስዎ የዘረዘሩዋቸው አብዛኞቹ ይህን ዓይነት መሪዎች አልነበሩም/አይደሉምም። የሲቪክ ማህበርና የፖለቲካ ድርጅትን ሚና ማደባለቁ ይጎዳል። ንቅናቄ በሚልም አጓጉል ፈሊጥ የድርጅትና የመደራጀትን አስፈላጊነት መሻሩ ወይም መፃረሩ ወይም የታገሉ ድርጅቶችን ማክቸልቸሉ ቀደም በተደጋጋሚ እንደታየው ለራስዎም ለሚያስቡትም ትግል ጠቃሚ አይደለም። እርስዎ አቶ ኦባንግ የሚወዱትና የሚደግፉት ድርጅት እንዳለ ለማወቅ አያዳግትም። በግልፅ ወጥተው ይደግፉትና ምላሽም ሌላም ይሰጥዎት። በሲቪክ ማህበር ስም ግን አሁን እየፃፉ ያሉት አሰባሳቢ ሳይሆን ከፋፋይ፣ጠቃሚ ሳይሆን ጎጂ፣ አንድነትን ሰባኪ ሳይሆን የቡድን ከለልተኛነትን አራማጅ ነው። አወቅኩ አወቅክ ሲሉት ቅዱስ መፅሐፍ አጠበ እንዳይሆንብዎ እሰጋለሁ። መድረክና ሀይ ሀይታ ብዙ ሰው ከእርስዎም በፊት አበላሽቷልና ጭብጨባችን እንዳያሳክርዎትና ግብዝ እንዳያደርገዎትም ፍርሀት አለኝ። ወጣ ወጣና ያልኩት በዚህ መንፈስ ነው።

ለመታረሙ ድፍረቱ ይኖርዎታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ሙሉጌታ አሻግሬ

ከምድረ ካሊፎርኒያ